# ሞዴል ለመሆን የበቃ መንገድ

**መሐመድ አወል**

በምእራቡ ዓለም የሚገኙ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በሰብአዊ መብት ጥበቃና በዴሞክራሲ ሥም ኢትዮጵያን ጨምሮ ልማታዊ መንገድን በሚከተሉ አገራት ላይ የምእራቡን ዓለም ርእዮተ ዓለም ለማንሰራፋት የተቻላቸውን ተፅእኖ ለማሳረፍ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ የራሳቸውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ሲሉ ብቻ የኒዮ ሊበራል ርእዮተ ዓለምን የማይከተል በምንም መልኩ ከኋላ ቀርነት አይወጣም፤ የኢኮኖሚ እድገትንም አይጎናፀፍም በማለት የሚሰብኩት እነዚህ ኃይላት ይህንን ግባቸውን ከዳር ለማድረስ የአገር ውስጥ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና በግብረ ሰናይ ሥም የተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ጭምር በህቡእ እየተጠቀሙ መሆናቸው ገሃድ የወጣ ሀቅ ነው፡፡

የኒዮ ሊበራል አራማጅ ኃይሎች እነርሱን ያልመሰሉና ፍትሃዊነት በጎደለው መልኩ ለሚሹት የኢኮኖሚ ጥቅም እንቅፋት ናቸው ብለው የፈረጇቸውን መንግስታት ጭምር በእጅ አዙር ለማስቀየር ጥረት አድርገዋል፤ በማድረግም ላይ ናቸው፡፡ ምንም እንኳ በአብዛኛው መና የቀሩ ቢሆንም ኒዮ ሊበራሎቹ  በዚህ ረገድ የወጠኗቸውና እየወጠኗቸው ያሉት ሴራዎች ከተሴሩባቸው አገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡

በአፍሪካም ሆነ በሌሎች በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ አገራት ከችግር መውጣት ያልቻሉት የምእራቡን ዓለም ዓይነት የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓትን እንዳለ በመገልበጥ በየአገሮቻቸው ባለመተከላቸው ነው የሚለው አስተሳሰብ ዘመናትን አሳልፏል፡፡ ሆኖም በምእራቡ ዓለም ስሌት አዳዲስ የዲሞክራሲ ስርዓትን የገነቡ የአፍሪካም ሆነ የእሲያ አገራት አንዳችም ለውጥ አላመጡም፤ ይልቁንም እጣ ፈንታቸው የእርስ በእርስ ጦርነት፣ የከፋ ርሃብና ስደት ሆኖ እስካሁንም ድረስ ዘልቋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ይህ ብሂራዊ ኃብት በጥቂቶች ቁጥጥር ስር እንዲሆን የሚያደርገውና በምእራቡ አገራት የተዘረጋው ልቅ የሆነ የገበያ ስርዓት ብዙሃኑን ህዝብ ለችግር የሚዳርግ መሆኑን ዓለም እየተገነዘበ መጥቷል፡፡

ከኒዪ ሊበራል ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ውጭ እድገት ማምጣት የሚቻል ብቻ ሳይሆን ርእዮተ ዓለሙ ዘላቂነት ላለው የተመጣጠነ እድገት የማይበጅ መሆኑ  መታየት የጀመረው ካለፉት ሁለትና ሶስት አስርት ዓመታት ወዲህ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የዚህ አስተሳሰብ ፈጣሪ የሆኑት አገራት ራሳቸው ተጠቂ መሆን ጀምረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢንዱስትሪ የበለፀጉትን አገራት ለታላቅ ፈተና የዳረገው የፋይናንስ ቀውስ ከዚህ አኳያ የሚጠቀስ ማሳያ ነው፡፡ ይህ ስር የሰደደ የኢኮኖሚ ቀውስ

የምእራቡ ዓለም የፖለቲካና ኢኮኖሚ ርእዮተዓለም የፈጠረው መሆኑን የሚያመለክት አስተያየት በተለያዩ የዓለም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አዋቂዎች ዘንድ እየተንፀባረቀ ነው፡፡

የምእራቡን ዓለም ዓይነት የካፒታሊዝም ስርዓት ወደጎን በመተው በየግላቸው ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት አገራቸውን ለመገንባት የጣሩ መንግስታት የተሻለ ውጤት በማሳየት ልቅ የሆነውን የገበያ ስርዓት የሚያራምዱ ክፍሎችን አስተሳሰብ ውድቅ ማድረግ ችለዋል፡፡ በዚህ ረገድ የሚያስደንቅ የኢኮኖሚ እድገት ያሳዩት ሲንጋፖርን የመሳሰሉ የሩቅ ምስራቅ አገራት ናቸው፡፡ እነዚህ አገራት የራሳቸውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት ያደረገን የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ በመከተል የህዝቦቻቸውን ህይወት መለወጥ ችለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ደግሞ ዓለምን ያስደመመ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እያሳየች የምትገኘው ቻይናም የምእራቡ ዓለም ርእዮተዓለም አብዛኛውን ህዝብ የማይጠቅም መሆኑን እያረጋገጠ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በጥቂት የአፍሪካ አገራትም ተመሳሳይ አስደማሚ እመርታ እየታየ መሆኑን ዓለም እየተቀበለው መጥቷል፡፡

ዎርልድ ፖለቲክስ ሪቪው (WPR) የተሰኘው ዓለም አቀፍ የምርምር ተቋም "The New Politics of African Development" በሚል አብይ ርእስ ያካሄደው ጥናታዊ ሪፖርት እንዳረጋገጠው ኢትዮጵያን ጨምሮ ጥቂት የአፍሪካ አገራት የምእራቡን ዓለም ዓይነት ስርዓት ሳይከተሉ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገቡ ናቸው፡፡

ተቋሙ ያወጣው ጥናታዊ ሪፖርት ኢትዮጵያን ጨምሮ በሩዋንዳና በኡጋንዳ ወቅታዊ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ጥናቱ ምእራባውያን ሁሉም የዓለም አገራት እንዲከተሉት የሚሹትና ያለማቋረጥ የሚሰብኩት የኒዮ ሊበራል ስርዓት በተለይ ኢትዮጵያን በመሳሰሉ የዓለም አገራት ውስጥ ሊሰራ እንደማይችል፤ አገራት ለህዝቦቻቸው ይበጃል የሚሉትን የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መንገድ መከተላቸው ለውጤት እንደሚያበቃቸው አብነቶችን በማቅረብ አረጋግጧል፡፡

ዎርልድ ፖለቲክስ ሪቪው (WPR) ላይ በቀረበው ጥናታዊ ዘገባ ላይ እንደተመለከተው ኢትዮጵያ የህዝቦቿን ህይወት ለማሻሻል በሚያስችል የእድገት ጎዳና ላይ ናት፡፡ አገሪቱ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ2006 እስከ 2010 ባሉት ዓመታት ውስጥ ብቻ አጠቃላይ ኢኮኖሚዋ በየዓመቱ ከ10 በመቶ በላይ እድገት አስመዝግቧል፡፡ ከ20 ዓመት በፊት ከስድስት ቢሊዮን የማይበልጥ የነበረው የዚህች አገር ብሄራዊ አጠቃላይ ገቢ (GDP) በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ2009 ወደ 17 ቢሊዮን ዶላር አድጓል ሲልም አመልክቷል፡፡

ጥናታዊ ሪፖርቱ የሚያሳየው የኢትዮጵያ መንግስት አገሪቱን ለዘመናት ከኖረችበት ድህነትና ኋላ ቀርነት ለማውጣት እየተከተለው የሚገኘው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት ለውጥ እያመጣ መሆኑን

ነው፡፡ ኢትዮጵያ የራሷን ተጨባጭ እውነት መሰረት በማድረግና ጠቃሚ የሆኑ የሌሎች አገራትን ተመክሮ በአግባቡ በመጠቀም ያመጣችው እድገት ማንም ሊያስተባብለው ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በዚህም የተነሳ አገሪቱ ለሌሎች መሰል አገራት ምሳሌ ልትሆን እንደምትችል ተሰሚነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና አገራት ጭምር በአደባባይ እየተመሰከረ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያን ጨምሮ ልማታዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መስመርን የሚከተሉ የዓለም አገራት በአሁኑ ወቅት እያስመዘገቡት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ኒዮ ሊበራል የፖለቲካና ኢኮኖሚ አስተሳሰብ በሁሉም የዓለም አገራት ውስጥ ሊሳካ የማይችል፣ ይህንን አስተሳሰብ መከተል በሁሉም የዓለም ህዝቦች ላይ የግድ እንዳልሆነ በግልፅ ማረጋገጡን የምእራባዊያን ምሁራን ሳይቀሩ መቀበል ጀምረዋል፡፡

ከዚህ እውነት ጋር በተያያዘ ያለውን አዎንታዊ ተቀባይነት ለማሳየት በአሁኑ ወቅት የአገራችንን የለውጥ ሂደት በተመለከተ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ የሚንፀባረቀውን አመለካከት ማጤን ይበቃል፡፡

በዓለም ላይ የሚታየውን የድህነት መጠን በግማሽ ለመቀነስ ይቻል ዘንድ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አማካኝነት የተቀረፀው የምእተ ዓመቱ የልማት ግብ ፕሮግራም ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ይህ ፕሮግራም በተገቢው መንገድ ስራ ላይ ከዋለ በየአገራቱ የሚታየውን የድህነት መጠን በግማሽ በመቀነስ የአብዛኛውን ህዝብ ህይወት በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል እንደሚቻል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ይገልፃል፡፡ ያም ሆኖ ግን ፕሮግራሙን የሚተገብሩት አገራት ግቡን ያሳኩ ዘንድ ቢያንስ በየዓመቱ ሰባት በመቶ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በሚያበረታታ ደረጃ ላይ መሆኗን የመንግስታቱ ድርጅት በተለያዩ ወቅቶች ባወጣቸው የምእተ ዓመቱ የልማት ግብ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ አስታውቋል፡፡ አገሪቱ በተለይ በተመድ ከተቀመጠው የእድገት መጠን በላይ እድገት በማስመዝገብ ላይ በመሆኗ የልማት ግቡን ሊያሳኩ ከሚችሉት ጥቂት የዓለም አገራት መካከል ለመጠቀስ በቅታለች፡፡ ይህም አገሪቱ እየተከተለችው የሚገኘው የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ስርዓት ውጤታማነትን የሚያንፀባርቅ መሆኑን ብዙዎች በመግለፅ ላይ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ መለያዋ የሆነውን ድርቅና ርሃብ ለማጥፋት እያደረገችው የሚገኘው ጥረትና እያሳየችው ያለው ለውጥም በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጭምር እየተነገረ ያለ ሌላው ስኬት ነው፡፡ መንግስት በአገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ስራ ላይ ያዋላቸው ፕሮግራሞች የአገሪቱ ምርታማነት እንዲጨምር አድርጓል፣ ይህንንም ተከትሎ በተፈጥሮ ችግር ሳቢያ የሚከሰትን ድርቅ መቋቋም የሚያስችል አቅም በአገሪቱ ተገንብቷል፣ ከእጅ ወደአፍ የነበረውን የአርሶ አደሩን ህይወትም ለውጧል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ እርዳታ ፕሮግራሞች ማስተባበሪያ ኃላፊ ሚስተር ጆን ጊንግ ሰሞኑን አዲስ አበባ ውስጥ በሰጡት መግለጫ የኢትዮጵያ መንግስት ባለፉት ዓመታት በወሰዳቸው የተለያዩ እርምጃዎች ሳቢያ በአሁኑ ወቅት አገሪቱ የድርቅን ተፅእኖ የመቋቋም አቅሟ በከፍተኛ መጠን አድጓል ብለዋል፡፡ ይህ በመንግስት ጠንካራ ቁርጠኝነት መሰረቱ የተጣለው ስትራቴጂ ለአፍሪካ ቀንድ ብቻ ሳይሆን ለተደጋጋሚ የድርቅ አደጋ ለሚጋለጡ የሳህል አገራት ሁሉ ሞዴል ሊሆን ይችላል ሲሉም የኢትዮጵያን ስኬት አወድሰዋል፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በፊት በኢትዮጵያ የስራ ጉብኝት ያደረጉት የዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ምክትል ዳይሬክተር ናኦዩኪ ሺኖሃራ የኢትዮጵያ መንግስት አገሪቱን መካከለኛ ገቢ ካላቸው የዓለም አገራት ምድብ ውስጥ ለማስገባት የሚያሳየውን ቁርጠኝነት በማድነቅ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ ምክትል ዳይሬክተሩ በዚሁ መግለጫቸው የኢትዮጵያ መንግስት በተለይ ካለፉት አስር ዓመታት ወዲህ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማጠናከር የወሰዳቸው እርምጃዎችና እየታየ ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ ነው፤ የአገሪቱ እድገት በዚሁ ከቀጠለ አገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው የዓለም አገራት የምትመደብበት ጊዜ ብዙ አይርቅም የሚል አስተያየትም ሰጥተዋል፡፡

በዚህም የተነሳ ልማትን በተመለከቱ ዓለም አቀፍ የፖለቲካና ኢኮኖሚ መስተጋብሮች ውስጥ ሁነኛ ስፍራ ባላቸው መድረኮች ላይ የአገራችን ስም እየተጠራ ነው፡፡ አገራችን የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን እንድታስተናግድ ተመራጭ እየሆነች ከመምጣቷም ባሻገር የዓለምን ህዝቦች በሚመለከቱ ልዩ ልዩ ጉባኤዎች ላይም ዋነኛ ተሳታፊ በመሆን ተመክሮዋን እንድታካፍል የምትጠራ አገር ሆናለች፡፡ ፡

ኢትዮጵያ በቅርቡ በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠውን የዓለም ኢኮኖሚ መድረክ አስተናግዳለች፡፡ በዚህ መድረክ ላይ የኢትዮጵያ ስኬት በተለያዩ አካላት በስፋት ተነግሯል፡፡ በመድረኩ ላይ ከታደሙት መካከል የዓለማችን ቁጥር አንድ ባለፀጋ የሆኑት ቢል ጌትስ በሰጡት አስተያየት በኢትዮጵያ እድገት እጅግ እንተደነቁና እንደረኩ ገልፀዋል፡፡

ቢል ጌትስ በኢትዮጵያ የለውጥ ሂደት ከልባቸው  መማረካቸው አስገድዷቸው ለተለያዩ ሚዲያዎች ባሰራጩት ፅሁፍ፣ "ወደ አፍሪካ በርካታ ጉዞዎችን አካሂጃለሁ፣ ነገር ግን በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ያደረኩት ጉዞ በጣም አስደሳች ነበር፣ … ለበርካታ ዘመናት ኢትዮጵያ ህዝቦቿን መመገብ ተስኗት የቆየች ሀገር ብትሆንም በቅርቡ በጤናና ግበርናው መስክ ያየሁት እድገት አስደስቶኛል፣ ለኢትዮጵያ እድገት አንዱ ምክንያት ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊና አመራራቸው የተጫወቱት ቁልፍ ሚና ነው፣ በአገሪቱ የሚታየው የልማት ስኬት ለሌሎች አገራት ሞዴል ሊሆን ይችላል፣" የሚል የአድናቆት አስተያየት አስፍረዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት የአገራችን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ግብዣ በቡድን ስምንት የበለፀጉ አገራት መሪዎች ጉባኤ ላይ ተሳትፈዋል፡፡ በጣት የሚቆጠሩ የዓለም መሪዎችን ባሰባሰበውና በምግብ ዋስትና ችግር ላይ በመከረው በዚህ መድረክ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የተጋበዙት በሚመሯት አገር የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የተዋጣለት ተግባር በመፈፀማቸውና ይህንኑ ተመክሯቸውን ለተቀረው የዓለም ክፍል እንዲያካፍሉ ተፈልጎ ነው፡፡ በዚህ ጉባኤ ላይም ተመሳሳይ አድናቆትን ነው አገራችን ያተረፈችው፡፡

ኢትዮጵያ በኒዮ ሊበራል ኃይሎች አማካኝነት ከየአቅጣጫው የሚተኮሱባትን ጥቃቶች መመከት የቻለችው የአገሪቱን ህዝቦች ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ የተከተለችው የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ስርዓት ውጤታማነት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ርሃብንና ድህነትን ለማጥፋት የተጀመረው ጥረትና እየታየ ያለው ለውጥ በራሱ አገሪቱ ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲሰጣት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ፡

ኢትዮጵያ የምትከተለው የእድገት መንገድና አዎንታዊ ውጤት የሚታይና የሚጨበጥ በመሆኑ ዓለም አቀፍ እውቅናን ተጎናፅፏል፡፡ ይህም በሰብአዊ መብት ጥበቃ ስም ሌላ የፖለቲካ ዓላማን የሚያራምዱ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ጭፍን ተቃውሞን የሚያራምዱት የአገራችን ተቃዋሚ ፖለቲከኞች አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ  መና መቅረቱን ያሳያል፡፡

በመሆኑም በተለይ የአገራችን ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ካለፉት 20 ዓመታት ጀምሮ ተጣብቷቸው ከኖረውና አንዳችም ትርፍ ካላገኙበት አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ መላቀቅ ያለባቸው ጊዜ አሁንም እንዳልዘገየ በመገንዘበ መስመራቸውን እንዲያስተካክሉ እመክራለሁ፡፡ ተቃዋሚዎቻችን የሚታገሉት የእውነት ለህዝብና አገር ጥቅም ከሆነ ከመንግስትና ህዝብ ጎን ሆነው ልናያቸው ይገባል፡፡ በፖለቲካ ሳይንስ አስተሳሰብ መሰረት የተቃዋሚ ፖለቲከኞች ሚና በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በሆነውና ባልሆነው ነገር ሁሉ መቃወም ብቻ አይደለም፡፡

ተቃዋሚነት በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ በዋና ዋና ሃገራዊ ጉዳዮችና አጀንዳዎች ዙሪያ ለሃገርና ለሕዝብ ፋይዳ ያለው የጠራ የጋራ አመለካከት መያዝ፣ በቀጣይም የተሻለና ተጨባጭ አማራጭ በማቅረብ ሕዝብን አሳምኖ ተቀባይነት በማግኘት አመኔታ ማትረፍ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ለመንቀሳቀስ ማሰብ የሕዝብና የሃገር ጠላትነት እንጂ ትክክለኛ የፖለቲካ ተቃዋሚነት ሊሆን አይችልም፡፡